# የውይይት መምሪያ ለቤተሰቦች

Reading Is Fundamental
until every child reads




**ሂድን ፊገርስ፤ ዘ ትሩ ስቶሪ ኦፍ ፎር ብላክ ዉመን ኤንድ ዘ ስፔስ ሬስ (Hidden Figures: The True Story of Four Black Women and the Space Race)**

*ደራሲ፤* ማርጎት ሊ ሽተርሊ (Margot Lee Shetterly)

*ሰዓሊ (Illustrator)፤* ላውራ ፍሪማን (Laura Freeman)

**ይዘቶች (Themes)፤** አካባቢ እና ዘላቂነት (Environment and Sustainability)

**የመጽሃፉ አጭር መግለጫ (Book Brief)፤** ዶርቲ ቮን (Dorothy Vaughan)፤ ሜሪ ጃክሰን (Mary Jackson)፤ ካትሪን ጆንሰን (Katherine Johnson)፤ እና ክርስቲን ዳርደን (Christine Darden) የዘር እና የሥርዓተ-ፆታ እንቅፋቶችን በማሸነፍ ለናሳ (NASA)ታሪካዊ የጠፈር ተልእኮዎች አስተዋፅዖ ያደረጉ ድንቅ አፍሪካዊ አሜሪካዊ የሂሳብ ሊቃውንት ነበሩ። ይህ የሥዕል መጽሐፍ በስቴም (STEM) ውስጥ ያላቸውን ጽናት፣ ትጋት እና ታላቅ ስኬት ያከብራል።

## ጮክ ብለው ያንብቡ (READ ALOUD)

**ከንባብ በፊት፤ መሰረት ይገንቡ (Build Background)**

- ልጅዎን "ዘራቸው፤ ባህላቸው፤ ሃይማኖታቸው እና ጾታቸው ምንም ይሁን ምን ሰዎች ስራቸው የመታወቁ አስፈላጊነት ለምንድነው ብለህ ታስባለህ?" በማለት ይጠይቁ

**በንባብ ወቅት፤ ግንኙነቶችን ይፍጠሩ (Make Connections)**

- ስለ ዶርቲ ቮገን (Dorothy Vaughano፤ ሜሪ ጃክሰን (Mary Jackson)፤ ካትሪን ጆንሰን (Katherine Johnson) እና ክርስቲን ዳርደን (Christine Darden) ምን እየተማራችሁ ነው? የልጅነት ልምዳቸው ትምህርታቸውን እና ህልማቸውን እንዴት ቀረፀው?
- ስእሎቹ የቃላት ዝርዝሩን እና ናሳ (NASA) በነበሩበት ጊዜ የ እነዚህ ሴቶች ህይወት ምን ይመስል እንደነበር ለመረዳት እንዴት ይረዳሉ?
- ከ1960ዎቹ ጀምሮ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በምህንድስና እና በሂሳብ ላይ ያሉ እድሎች የበለጠ ፍትሃዊ ሆነዋል ብለው ያስባሉ? ምን ምሳሌዎችን ማሰብ ይችላሉ?

**ከንባብ በኋላ፤ ጥያቄዎች ይጠይቁ**

- በመጽሐፉ ጀርባ ያለውን ተጨማሪ መረጃ ተመልከት። በናሳ (NASA) ውስጥ የእያንዳንዷ ሴት ልዩ ሙያ ምን ነበር,? እና ለየትኞቹ ዋና ዋና ፕሮጀክቶች አስተዋፅኦ አድርገዋል? ሥራቸው ታሪክን ለመቅረጽ የረዳው እንዴት ነው?

## ተዛማጅ ተግባራት

**ልጅዎ ይህን መጽሃፍ ከወደደ፤ የሚከተሉትን ከግምት ያስገቡ፤**

- በሌሎች ንግግሮች ጊዜ ስለ እሱ እንዲያወሩ አበረታቷቸው።
- በተዛማጅ መጽሃፍት እና ሪሶርሶች (resources) ስለ ዘላቂነት (sustainability) የበለጠ ለማወቅ የአር አይ ኤፍን (RIF's) Sustainable Futures ማዕከልን ይመልከቱ።


©2024 Reading Is Fundamental